«ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።» ማቴ. 24

# ምጽአቱ ደረሰ

ምጽአቱ ደረሰ ጌታ የሚመጣበት
ጻድቃን አክብሮ ዋጋ የሚሰጥበት
ኃጥአኑን ኰንኖ ቀጥቶ የሚልክበት።

ምጽአቱ ደረሰ ትንቢት ተፈጸመ
ሰው ግን በኃጢአት በተንኮል ተመመ
አልመሰሰ ብሎ በዓለም ከተመ።

ምጽአቱ ደረሰ ምንድን ነው ጥበቃው
ከዓለም ተለይተህ ዛሬ የማታመጣው
ቀናን መንገድ ይዘህ ከቶ የማታቀናው።

ምጽአቱ ደረሰ የሚዘመርበት
የጌታችን ግርማ የሚገለጽበት
የጻድቃን ሥራቸው ጉልቶ የሚደምቅበት
የኃጥአን ልቅሶ ዋይታ የሚሰማበት።

ምጽአቱ ደረሰ ኢለም ኢለም የምታልፍበት
መብልና መጠጡ የሚፈጸምበት
ማግባት መጋባቱ ኑሮ የሚያበትምበት።

ምጽአቱ ደረሰ ምድር ተናወጠች
በዓለሙ ዙሪያ ምልክት አሳየች
የጌታ ቀን መምጫው እኮ ደረሰ እያለች።

ምጽአቱ ደረሰ አሳቾች ተነሱ
የሐሰት ካባ ለብሰው ፈጥነው ገሠገሡ
እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ እናፈሱ።

ምጽአቱ ደረሰ ጦርነት ተሰማ
የአዳም ፍጥረት ሁሉ ለእውነት አቅማማ
ወንድሙን በከንቱ እያነሳ እያማ
ንጹሑን ሕሊና ደረሰ እያደማ
በግፍ በጭካኔ ገድሎ እየቀማ።

ምጽአቱ ደረሰ ራብ ቸነፈር መጣ
ፍቅርም ከሰመች መተማመን ታጣ
አንዱ ሌላኛውን አሳልፎ አወጣ።

ምጽአቱ ደረሰ ጨረቃ ልትጨልም
የሌሊት ብርሃኗን መሰጠቱ ሊያበትም
የፀሐይ ሙቀትም ሊጠፋ ሊወድም።

ምጽአቱ ደረሰ ከዋክብት ሊወድቁ
ከእንግዲህ በሰማይ ዳግመኛ ሳይደምቁ
ጌታ እንደየሥራቸው ፍጥረታት እንዲያውቁ።

ኃይለ መስቀል ተሰፋዬ -
ለንደን
ነሐሴ 1996